# ተዓምረ ሎሚ ሽታ
**በMark O's**

## መግቢያ

መስመሮቻችን ምናልባትም ቀጥታ አይደሉም፡፡ ጥምዝ ወይ ክብነት የሚያጠቃቸው ናቸው። እየተነሱበት ላይ ዞሮ የመድረስ ምስጢር እዚህ ላይ ይሆናል። የየነጠላው ጉዞአችን ዑደት የተጠላለፈ ሰንሰለት የሚሰራ ነው፡፡ እዚህ ስንጀምረው እዚያ በሌላ ክብ ላይ የሚቋጭ.... የራሳችን እንደሆንን ሁሉ የብዙሃኑ ውጤትም ነንና።

መጠላለፋችንን አናውቅም፡፡ ህይወታችን በዑደት የተሞላ እንደሆነ ብንገነዘብም ግን ዑደቶቻችን እንደተጠላለፉ አንረዳም፡፡ ትናንት የተለየነውን ነገ በሌላ ዑደት ዞረን እንደምንገጥመው አናውቅም፡፡
እዛ እና እዚህ የረሳናቸው ደቂቅ ትዝታዎች በሆነ አጋጣሚ ይመለሳሉ፡፡ እዚያ ያቆምነው እዚህ ይቀጥላል፡፡ ዘጋናቸው ያልናቸው ምዕራፎች ይቆላለፋሉ በመቆላለፋቸው ውስጥ እየተጠመጠሙ በህይወታችን ያንዣብባሉ፡፡

'ሎሚ ሽታ' የራሱ ጉብታዎች፥ ሸለቆዎች፥ ጎጆዎችና ጎዳናዎች ያሉት መኖር ነው። ያልተነገረ ታሪክ የለም። ያልተኖረም ህይወት ብንል ያላስተዋልነው እንደማይጠፋ እነዚህ የነጠላ መኖር ሁነቶች ላይ ህይወት የዘራው ትሥሥር ይነግረናል። ካላየነው፥ አይተን ቸል ካልነው፥ ከዘነጋነው ላይ ለግዙፉ መሆን ዓለምን ያህል አመክንዮ የያዘች ረቂቅ ትስስር አለች።

**'ሎሚ ሽታ' መኖርን ነው።**

ደራሲ አዳም ረታ ከላይ በመንደርደሪያው ተቀንብቦ ለመጥቀስ በተሞከረው 'እቴሜቴ ሎሚሽታ' በተሰኘ የ319 ገጽ ዕድሜ ያለው የአጫጭር ልብ ወለዶች ስብስብ መጽሐፍ ላይ 'ግራጫ ቃጭሎች' በሚል መጽሐፉ ያስተዋወቀንን የ'ሕጽናዊነት' አጻጻፍ ቴክኒክ በአግባቡ ተጠቅሞበት እናያለን። ሕጽናዊነት በአጭሩ የተለያዩ ታሪኮችን ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ባለሆነ ትሥሥር የማገናኘትና ግንኙነታቸውን አጉልቶ ማሳያ ቴክኒክ ነው።
ሎሚ ሽታ በተሰኘው በዚህ መጽሐፍም እነዚሁ አጫጫር የታሪክ ጉብታዎች ቀጥተኛ ባልሆኑ ስውር ትስስሮች ተቆላልፈው አንድ ወጥ የሆነ ታሪክ ሲቀርጹ ይታያል። ከዚህ በተጨማሪ አንደተራኪያቸው እይታ እና አንደታሪኮቹ ጉብታ መለዋወጥ የታሪኮቹ ጭብጥም ይለያያል። ገጸባህርያቱም የየራሳቸውን አንዳች ጽንሰሐሳብ ወክለው እናገኛቸዋለን። የአተራረክ ዝርዝና ጥልቅ ትነታኔዎች አተኩሮ ለስሜት መቅረብና ሥነጽሑፋዊ ለዛውም እዚህ መጽሐፍ ላይ የበለጠ ረቅቆ ይገኛል። ከዚህ በታች እነዚህኑ እንዳስሳለን።

**[ስለ'ሊጋ አቅሚቲ']**

አዳም ልጅነትንና አፍላነትን ጠለቅና ዘርዘር የአጻጻፍ ውበት ከአእምሮአቸን የማይጠፉ ትውስታዎችን እየቀሰቀሰ የማስቃኘት ልምዱን እዚሁ መጽሐፍም ላይ ተጠቀሞበታል። ትዝታዎች ጋር የመጫወት አቅሙን በመጠቀም ወደምንወደውና መሠረታዊ ትውስታዎቻቸንን ወደገነባንበት የለጋነት ጊዜአቸን መለስ ያደርገናል።

**(እቱ ኮረሪማ)**

.."ደረሰ" "ደረሰች" ምን ጋ ደረስን?...
አፍላነታችን የመንገዱ መንደርደሪያ ነው። በትኩሣት ሁሉን የምናስስበት፤ የከባችንን ውስጥና ውጪ የምንገነዘብበት

ኮረሪማ ጠይም ልጃገረድ ነች፤ ወዳጇ 'ጠይም ጦር' የሚላት ተወርውራ በዐይን የምትገባ። እሱ፥ እንደሷ በአፍላነት ያለ ስለማደግ የሚያሰላስል። አፍላነትን ታክኮ የያዛቸውን መውደድ፥ የተቃጠሩትን መቃጠር በ'ደረሰ' 'አደገ!?' ከበቡ አሽሙር ቢጤ እንዳይቀባቡባቸው ከቡ በሰጣቸው መሽኮርመም የተኳለ ቴክኒክ ብጤ ለመፍጠር ይጥራሉ።

**..."ሦስቴ አፏጭልኝ"... ላባ ፉጨቶች**

ለጋ አእምሮ በጥያቄ የተሞላ ነው። ተራውን፥ ኢምንቱን እየፈለፈለ በሐሳብ ይዋልላል። ተራኪያችን እዚህና እዚያ በሐሳብ ይዋትታል። ጉጉት አለበት። እንደሷ የጣፈጠ ነገር ሊጋብዛት፤ ከናፍሯን ሊስም፤ ሰው አየን አላየን ሳይሉ፤ 'ደረሱ' ተብለው ተገፍተው የጎረመሷት መጎርምስ የመቃመስ። ጉጉት!

አዳም በዚህ 'መቼ ትመጣለህ?' በተሰኘ ትረካው። ጉጉትና ፍርሃት ከማህበረሰባዊ ከበብ ጋር የሚፈጥሩትን ድብብቆሽ ነጸብራቅ አድርጎ አፍላነትን ያሳየናል። ሐሳቡ ከረር ሲልም ከሞራላዊ የማህበረሰብ እሳቤ ጋር አያይዞ ልጆች ከበድ ባለ ቁጥጥር የማሳደግ ባህላችንን ተቸት ያደረገበት ሆኖ እናገኘዋለን።

**('ውስጥ ሱሪዎች')**

"ገዳምሽ እይ..."
ገዳም ማርታ የሚሏትን ጉብል የሚወድ ሌላ አፍላ ነው። ተነግሮን የማንማራቸው፤ ለጋነት ከዙሪያችን የሚያስቃርመን፤ ትናንሽ ብልግና ብጤ ፈንጠዝያዎች ቀምሰን የሳቅንባቸው፥ አይተን

እየጎሻሸምን ያውካካንባቸው እና ደግሞ ምናልባትም እያየን እየኖርናቸው ቸል ያልናቸው (በመደበቅ፥ በመሸፋፈን ስልት) እነዚያን ያስቃኘናል።

የልጅነት ፍቅሩን ከትምህርት ቤት ወዳጆቹ፥ ከሠፈሩ ጋር ስላለው የተሳሰረ መኖር። ዐይኑ ሽረፍ አድርጎ ካያቸው 'ሁለት ተኩል የውስጥ ሱሪዎች' እና ቦለሌ በሚያከሉ የራሱ ውስጥ ሱሪዎች አስተክኮ እየተረከ ልጅ በመሆን መሽኮርመም ተድበስብሰው የሚያልፉ ትውስታዎችን ይቀሰቅሳል።

'በዚህ ሁለት ተኩል ውስጥ ሱሪዎች ለአዲስ አበባ' የተሰኘ ትረካ ውስጥ አዳም በፍቅር የመፈላለግን ውብ ጊዜ አስታክኮ ከወጣትነት ጋር የሚመጡ ፖለቲካዊ ትኩሣቶችን እና አፍላነት ለመቀበል ያለውን ቅርብነት ሊያንጸባርቅልን ይጥራል። አዳዲስ ፍልስፍናዎችና ኩሽቶች፥ ቧልትና ተድበስብሰው የሚደረጉ ስድ መሳይ ነገሮችን ሳይቀር በችኮላ የመቀበያ ጊዜ የሆነው ወጣትነት እዚህ ታሪክ ላይ ቀርቧል።

**[እውነት፥ ተረት፥ ምናብ]**

አዳምን ከሚያገዝፉት የሥነጽሑፍ ጥራቶቹ አንዱ ምናቡ ነው። ተራ ነገሮቸን የሚያገዝፍ ፋንታሲ እና ግዙፍ ነገሮችን ተራ አድርጎ የሚያስተሳስር እውነታ የመፍጠር ልምድ አለው። ነገሮችን ከየራሳቸውን የትረካ ጉብታ ላይ እንድንፈርጅ የሚያስችል ጽሑፍ ማቅረቡም ይሄንኑ ፋንታሲ በአግባቡ እንዲጠቀም ነፃነት የሠጠው ይመስላል።

በ'እቴሜቴ ሎሚ ሽታ' መጽሐፍ ላይ በእውን ዓለም የታወቁ ሰዎች ምናባዊ ገጽታ ተጨምሮባቸው ቀርበዋል። ከዚህም በላይ በእውኑ ዓለም የሌሉ መጻሕፍትና መዛግብት እንደማጣቀሻ ቀርበው ከጀርባ ገጽ ላይ የምናብ ማጣቀሻለዎች ተብለው መቅረባቸው ያነሳነው ነጥብ ሌላ ማሳያ ነው።

**(የስብሐት ጢም)**

"በቃ። ጥረቱ ይፃፋል። ሁሉ ነገር ጥረት። ሰው ሞትን በተለያየ ጊዜ በተለያየ ስልት በዓመታት፥ በሰዓታትና በደቂቃ ይሸውዳል።"

በዚህ የመኖር ጉብታ ደራሲው እውነታው ዓለም ላይ ያለ ገጸባህርይን ተረታማ ፈጠራ አለባብሶ ያቀርብልናል። ከሰማነው፥ አንብበን እና አይተን ካወቅነው ስብሐት በዘለለ ምናባዊና ተረታማ ባህርያት በመፍጠር ይራቀቃል። ስብሐት ነበልባል የሚኔቀለቀልበት ጢሙን ለድርሰት መንፈሱ መነሳሻነት ሲጠቀም እያየን እንደመማለን። ከዚህም በላይ ስብሐት ባይተዋር ሲቀር

ከሚመጣለት የጽሑፍ መንፈስ መነቃቃት ተነስተን ደራሲው በመተሳሰር ውስጥም ላለ ግለኝነት/ Individualism የሰጠውን ግዘፍ እንመለከታለን።

**(መስኮትና ብሩሽ መጣል)**

መስኮት የስብሐት ወዳጅ የሆነ ሠዓሊ ነው። በዚህ ሠዓሊ የአሳሳል ጥበብ ዳሰሳ ውስጥ ደራሲው ስዕል በሥነጽሑፍ ጎልቶ መታየት እንደሚቻል ያሳየናል። መስኮት አዳም ረታ ከደራሲነት ወደሐያሲነት የሚንሸራተትበት ጎዳና ሆኖ ያገለግላል። መስኮት ተነካናኪ የሚባል የብሩሽ አጣጣል(የአሳሳል) ፍልስፍና አግኚ ሆኖ ቀርቧል። በተነካናኪነት ፍልስፍናው የተማረኩ ወጣቶች መወያያ ሆኖም በሌሎች የትረካ ጉብታዎች ላይ ተጠቅሷል። በተነካናኪ ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ ሁሉ ነገር ብዙ ጎን አለው የሚል ሐሳብ ጎልቶ ይንጸባረቃል።

አጭሩ ሠዓሊ መስኮት ተራ ገጸባህርይ መስሎ ገብቶ በጎዳግ ጽሑፎች እየገባ የጉብታዎቹ ዋነኛ መተሳሰሪያ ገመድ ሆኖ ይገኛል። በተጨማሪም በመስኮት ገረሱ የሐያሲነት ባህርይ ተነስቶ ደራሲው ከረር ያሉ ማሕበረሰባዊ ሂሶቹን ይሰነዝራል። ከዚህም ባለፈ ቅይጥና ዘፈቀዳዊ ስለሚመስሉ 'contemporary' የኪነጥበብ ውጤቶች ውበት ያንጸባርቃል። በዚህም ከተኳኳለ ሀቅ በላይ ግርድፉ ተፈጥሮኣዊ እውነታ ላይ ብርሃን ለማንጸባረቅ የጣረ ይመስላል።

**[ሾላ'ፍና ነገረ ማድያት]**

"እኔ ስለሾላ ሳወራ እንደማገኛውም ሰው በአእምሮዬ የሚመጣው ልጅነቴ፥ ደንና ባላገር ነው።" አዳም ረታ በመሠረታዊነት በሥነጽሐፍ ስራዎቹ የኤግዚስታንሺያሊስም ፍልስፍና ይጸባረቅበታል። የሕይወት ከንቱ መሆንን በመታዘብም ሆነ በተራ ድብርት ውስጥ የመኖር ጣዕማቸውን በማጣትና ዳግመኛ በመፈለግ መሐል የተጠመዱ ገጸባህርያትን በመጽሐፉ እናገኛለን። በመበደል ክር የተሳሰሩ ገጸባህርያትን አቅርቦ የእውነት ነጭና ጥቁር ዋልታዎች እንደሌሉና ነገሮች በሁለቱም እውነት ቅይጥ ግራጫ ላይ እንደሆኑ ያሳየናል። ቀለመወርቅ በልጆቿ ትይዩ ተንጸባርቃ ወጣትነቷን መለስ ብላ ልታሳየን የቀረበች ፅፀትን የወከለች ገጸባህርይ ነች። ደራሲው በዚህችው ገጸባህርይ የባልትና ሙያ ውስጥ ለከበቡ ትውፊታዊ መልክ የሚሰጥ Recipe ለመፍጠር ይሞክራል።

**የሾላ ፍርፍር!**

በቋንጣ ወይም በሥጋ ምትክ በፀሐይ የደረቀ ሾላ ፍሬ ተቁላልቶ የሚገባበት ምግብ። ሾላ'ፍ ሎሚሽታ ላይ ላለ ህይወት ባህላዊ እሴት ለማከል የገባ ማጣፈጫ ነው።

በባሏ ላይ ለአፍታ የወሰለተችው የአጭር ጊዜ የህይወት ዘመን ፀፀቷ አፍንጫዋ ላይ ባለማድያት (የደበቅነው ሁሉ በሌላ መንገድ ራሱን ብቅ ያደርጋልና) ተገልጦ ይታያል።

'እንደኩኒፎርም ቢነበብ ማድያቱ ድርሳኗ ነው።' ይለናል ደራሲው። ሀቁ ላይ እና የምንዳስሰው ላይ ከማተኮር አልፎ Superstitious ወደሆኑት ማህበረሰባዊ እሴቶቻችን ይዘልቃል። በምናደርጋቸው መጥፎ የተሰኙ ነገሮች ስለሚደርስብን 'ካርማ' እና ቅጣትንና በደልን እያጣጣሙ ስለመኖር ሳይቀር እያነሳ የህይወትን Grey መሆን ያንጸባርቃል።

[ያልተነገረን ወይ ልብ ያላልነው]

**-ፀጥታ ነጋሲ-**

"ይሄ አብዛኛው የምንኖርበት ዓለም ፀጥታ ነው። ያልተነገረለት ነው"
ታሪክ ዘመን በመቁጠር እና ጠጣሩኔ የታየ ነገር ከመመዝገብ ባለፈ። ሰዎችን እንደሰው ከነሰበራታቸው አለመሳሉን ደራሲው ጠቆም ያደርገናል እዚህ ላይ።
ያልተነገሩንን በምናቡ ያስሳል።

አይተን ያላስተዋልናቸውን ቢሆኑስ ይለናል።

ያየነውን የሰማነውን እንመርምር እስቲ ሁሉ እንደምናየው፥ እንደሰማነው ነውን?
ሎሚ ሽታ ለአዳምና ሔዋን፥ ለሙሴ ለሰሎሞን እንኳን ሳይመለስ ያልሰማነውን ሊቃኝ ምናቡን ከታየው ጀርባ ስላለው ያልታየ እውነት ይልካል።

አዳም በዚህ 'ፀጥታ ነጋሲ' የተሰኘ ንዑስ ርዕስ ሥር በጻፈው ትረካና ገለጻ ባህላችንና ኃይማኖታዊ ትውፊቶቻችን የሚያኖሩብንን ሰውን እንደሰው ያለመመልከት አባዜ ጠቆም አድርጎ ለሕሊና ትችት ክፍት ያደርጋቸዋል። የምናውቃቸውን ታሪካዊ መረጃና ማስረጃዎች ከስንት የትረካ አቅጣጫ እና ከስንት የእውነት መስመሮች አንጻር እንዳተመለከተናቸው መለስ ብለን እንድንመረምር የሚይጠይቅ ትንሽ ሙግት ቢጤ ያጭርብናል።

**[እቴሜቴ..]**

"ዕብድ ማለት በቀጫጫ አጀንዳ ወፍራም ሞት መስራት ነው!"

ሟች እናቱ በአሉባልታ ባሏንና ጤናዋን ተነጥቃ ነው ያለፈችው። ሚስቱ ሎሚ ሽታ ጥላው ኮብልላለች። ታደሰ መበደል እና ቅጣትን ሆኖ ቀርቧል። ስለበደሉ እናቱን፥ ሎሚሽታን፥ ሁላገርሽን፥ ራሱንና ዓለሙን ሁሉ የሚቀጣው በዝምታ ነው።

'እንዳሻቸው ይሁኑ!' ማለትን ያህል ቅጣት ፈልገን እስክናጣ በዚህ ጉብታ ደራሲው ዝምታን ጅራፍ ሆኖ ተገምዶ ሲቀርብ ያሳየናል። (ስልጣኑ ከማሳየት የዘለለ አይደለምና..)

ከላይ የጠቀስነው የበደል ትሥሥር ጎለብቶ የሚታየው እዚህ 'እቴሜቴ ሎሚሽታ' የተሰኘ ታሪክ ላይ ይጎላል። ደራሲው ለአሉባልታ ያለንን ግዙፍ ቦታ በታሪኩ ያሳየናል። ከዚያም አልፎ የማሕበረሰብ ተጽዕኖ በተለይም በመገፋት ብዛት ከሚፈጥራቸው የራሱ መጥፎች አንጻር እያነሳ ያሳየናል።

**=መደምደሚያ=**

[ሎሚ ሽታ_ስውር ሥፌት]

-ምትሐቱ ሲገለጥ-
አዳም ሕጽናዊነትን በቀደመ መጽሐፉ 'ግራጫ ቃጭሎች' አስተዋውቋል። 'ሎሚ ሽታ' በሕጽናዊነት የሚገለጸው የነገሮች ረቂቅ ትስስር ስውርነት በቴክኒኩ ውስጥ ተሰውሮ የመጣበት ነው።

መስኮት ገመድ ሆኖ ቀርቧል። ሁነቶች ሠንሰለቶች ሆነው ቀርበዋል። መስኮት እና ሁነቶቹ የሚፈጠሩበት መቼቶች የዚህ አጭር ልበወለዶች ተገጣጥመው የሚሰሩት የወጥ ታሪክ ምትሐት ላይ ዋና ገጸባህርይ ሆነው ይመጣሉ። (እዚህ ጋር አጽንዖት እንሰጣለን! መቼት ገጸባህርይ ሆኖ አገልግሏል።)

የታሪክ ጉብታዎቹ የተሰሳሰሩበት ሰንሰለት ስውር ጥልፍልፍ ስለሆነ ሳያደናቅፈን፥ ሳይጎረብጠን ፍስስ ብሎ ይነበባል።

'ሎሚ ሽታ' እንደመኖራችን ነው።

መተሳሰራችንን አናስተውልም። የእኛ እንደሆንን ሁሉ የሁሉም የሚያደርጉን የሚያስተሳስሩን መስመሮች ስውር ናቸው። ካላየነው፥ አይተን ቸል ካልነው፥ ከዘነጋነው ላይ ለግዙፉ መሆን ዓለምን ያህል አመክንዩ የያዘችን ረቂቅ መጠላለፍ ጉልህ ነፍስ በዚህ መጽሐፍ ተዘርቶባት እናያለን።

'ሎሚ ሽታ' መኖርን ነው!

በሎሚ ሽታ ውስጥ የሚታየው ትሥሥር አዳም ማሕበረሰብ ከግለሰብ ግለሰብ ከማሕበረሰብ ጋር ያላቸወን ሰብጀክቲቭና ኦብጀክቲቭ መስተጋብር አግዝፎ ያሳየበት ነው። አካባቢያዊ ተጽዕኖ የግለሰብ ሕይወት ቀረጻ ላይ ስለሚጫወተውን ሚና እና የግለሰብ ተሳትፎ ማሕበረሰብ ውስጥ ስለሚኖረው አስተዋጽዖ በውብ የአጻጻፍ ለዛ ግዙፍ ፍልስፍና አኑሯል።

አዳም በሎሚ ሽታ ላይ የሚፈጥርልን ትሥሥር እንግዳ ሳይሆን የምናውቀውን የማግዘፍ እና ባላየንበት አቅጣጫ የማመልከት ባህርይ ያለው በመሆኑ መጽሐፉ ለልብ የቀረበ ሆኖ አናገኘዋለን። ለዚህም ነው በመግቢያዬ 'ሎሚ ሽታ' መኖርን ነው ያልኩት፤

ስደመድምም እንዲሁ… መኖራችን ከትሥሥር ውጪ አይደለምና።